የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

| አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፴፮<br>አዲስ አበባ መጋቢት ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም | በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ<br>የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 10th Year No. 36<br>ADDIS ABABA-25th March, 2004 |
|---|---|---|

## ማውጫ

**አዋጅ ቁጥር ፫፻፺፮/፲፱፻፺፮ ዓ.ም**

የኢጋድ አባል ሀገራት በይነ-ፓርላሜንታዊ ኅብረት መመስረቻ ፕሮቶኮል ማጽደቂያ አዋጅ...... ገጽ ፪ሺ፮፻፱

## CONTENTS

**Proclamation No. 396/2004**

Protocol for the Inter-Parliamentary Union of IGAD Member States Ratification Proclamation ..... Page 2609

### አዋጅ ቁጥር ፫፻፺፮/፲፱፻፺፮

### የኢጋድ አባል ሀገራትን በይነ-ፓርላሜንታዊ ኅብረት መመስረቻ ፕሮቶኮል ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

የኢጋድ አባል ሀገራት ርዕሳነ ብሔራትና መስተዳደራት ባካሄዱት ፰ኛ መደበኛ ጉባዔ እ.ኤ.አ. ኖቬምበር ፳፫ ቀን ፪ሺ ባወጡት የካርቱም ዲክላሬሽን የአባል ሀገራቱ በየነ-ፓርላሜንታዊ ኅብረት ይመሠረት ዘንድ ሀሳብ ያቀረቡ በመሆኑ፤

ለበይነ-ፓርላሜንታዊ ኅብረቱ ምስረታ እ.ኤ.አ. ፌብርዋሪ ፳ ቀን ፪ሺ፬ አዲስ አበባ ላይ የተሰበሰበው የኢጋድ አባል ሀገራት ብሔራዊ ፓርላማዎች የአፈ-ጉባዔዎች ሸንጎ የኅብረቱን መመስረቻ ፕሮቶኮል የተቀበለው ስለሆነ፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የኅብረቱን ዓላማዎች ሙሉ በሙሉ የሚደግፍ በመሆኑ፤

ፕሮቶኮሉ በሥራ ላይ የሚውለው ከኢጋድ አባል ሀገራት ብሔራዊ ፓርላማዎች መካከል አራቱ ሲያጸድቁት እንደሆነ በፕሮቶኮሉ የተመለከተ በመሆኑ፤

### PROCLAMATION NO. 396/2004.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE PROTOCOL FOR THE INTER-PARLIAMENTARY UNION OF IGAD MEMBER STATES

**WHEREAS,** the Heads of State and Government of IGAD Member States had proposed for the establishment of an Inter-Parliamentary Union of IGAD Member States in the Khartoum Declaration they issued at their Eighth Ordinary Summit held on 23rd November 2000;

**WHEREAS,** the Conference of Speakers of National Parliaments of IGAD Member States that convened in Addis Ababa, on 20 February 2004, for launching the Inter-Parliamentary Union has adopted the Protocol thereof;

**WHEREAS,** the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia fully endorses the objectives of the Union;

**WHEREAS,** it is stipulated in the Protocol that it shall enter into force upon ratification by four National Parliaments of the Member States of IGAD;

ይኸንኑ ፕሮቶኮል የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

## ፩ አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢጋድ አባል ሀገራት በይነ-ፓርላሜንታዊ ኅብረት መመስረቻ ፕሮቶኮል ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፺፮/፲፱፻፺፮ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## ፪ ፕሮቶኮሉ ስለመጽደቁ

የኢጋድ አባል ሀገራት በይነ-ፓርላሜንታዊ ኅብረት መመስረቻ ፕሮቶኮል በዚህ አዋጅ ጸድቋል::

## ፫ አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከመጋቢት ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ መጋቢት ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has, at its session held on 25th March 2004, ratified the said Protocol;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Sub Article (1) and (12) of Article 55 of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Protocol for the Inter-Parliamentary Union of IGAD Member States Ratification Proclamation No. 396/2004".

## 2. Ratification of the Protocol

The Protocol for the Inter-Parliamentary Union of IGAD Member States is hereby ratified.

## 3. Effective Date

This Proclamation shall come into force as of 25th day of March, 2004.

**Done at Addis Ababa, this 25th day of March, 2004.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት